የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 36
ADDIS ABABA 22nd May, 2014

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፫፻፰/፪ሺ፮ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ....ገጽ ፯ሺ፫፻፺፪

CONTENTS

Regulation No. 308/2014

Ethiopian Energy Authority Establishment Council of Ministers Regulation.... ..........................Page 7392

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፰/፪ሺ፮**

**የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና አንቀፅ ፴፬ እንዲሁም በኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ አንቀጽ ፫ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፰/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣

፩/ "አዋጅ" ማለት የኢነርጂ አዋጅ ቁጥር ፰፻፲/፪ሺ፮ ነው፤

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፪ የተመለከቱት ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 308/2014**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN ENERGY AUTHORITY**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 and Article 34 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 3 of the Energy Proclamation No. 810/2013.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Energy Authority Establishment Council of Ministers Regulation No.308/2014".

2. **Definitions**

In this Regulation unless the context otherwise requires:

1/ "Proclamation" means the Energy Proclamation No. 810/2013;

2/ the definitions provided for under Article 2 of the Proclamation shall be applicable;

ያንዱ ዋጋ
Unit price 5.25

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩

፫/ "ሚኒስቴር" ማለት የውሃ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው ፤

፬/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

**፫. መቋቋም**

፩/ የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።

፪/ ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል።

**፬. ዋና መሥሪያ ቤት**

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

**፭. ዓላማ**

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል ፡-

፩/ የኢነርጂ ዘርፉን ተወዳዳሪነት ማበረታታት ፤

፪/ ብቃት ያለው፣ አስተማማኝ፣ ፍትሐዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ከአደጋ ነፃ የሆነ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ማረጋገጥ ፤ እና

፫/ የኢነርጂ ብቃትና ቁጠባን ማስፋፋት።

**፮. የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር**

የባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል ፡-

፩/ በአዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱትን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል ፤

፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

3/ "Ministry" means the Ministry of Water, Irrigation and Energy;

4/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. Establishment**

1/ The Ethiopian Energy Authority (hereinafter the "Authority") is hereby established as an autonomous federal government office having its own legal personality.

2/ The Authority shall be accountable to the Ministry.

**4. Head Office**

The Authority shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as necessary.

**5. Objectives**

The objectives of the Authority shall be to:

1/ promote competitiveness in the energy sector;

2/ ensure efficient, reliable, fair, economical, and safe electricity supply; and

3/ promote energy efficiency and conservation.

**6. Powers and Duties of the Authority**

The Authority shall have the powers and duties to:

1/ exercise the powers and duties provided for under Article 4 of the Proclamation;

2/ own property, enter into contracts, sue and be sued in its own name;

፩/ ቦርዱ በየሁለት ወሩ አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል።

፪/ በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።

፫/ የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ላይ ከተገኙ አባላት በአብዛኛው ድምጽ ሲደገፍ ነው፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

## ፲፩. የዋና ዳይሬክተሩ ሥልጣንና ተግባር

፩ ዋና ዳይሬክተሩ የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሆኖ ከሚኒስቴሩ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑ ሥራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዳይሬክተሩ ፦

ሀ) በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 የተጠቀሱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) የባለሥልጣኑን ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት እንዲሁም የባለሥልጣኑን ዓላማ በማስፈጸም ሥራ ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎችን የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፡

1/ The Board shall meet once every two months; provided, however, that it may hold a meeting at any time when necessary.

2/ The presence of more than half of the members at any Board meeting shall constitute a quorum.

3/ Decision of the Board shall be passed when supported by majority vote of members present at the meeting; provided, however, that the Chairperson shall have a casting vote in case of a tie.

4/ Without prejudice to the provisions of this Article the Board may adopt its own rules of procedure.

## 11. Powers and Duties of the Director General

1/ The Director General shall be the chief executive officer of the Authority and shall, subject to the general directions of the Ministry, direct and administer the operations of the Authority.

2/ Without limiting the generality of sub-article (1) of this Article, the Director General shall:

a) exercise the powers and duties of the Authority referred to in Article 6 of this Regulation;

b) employ and administer employees engaged in support services of the Authority in accordance with the federal civil service laws and, in the case of professionals engaged in the core functions of the Authority, in accordance with directives approved by the government following the basic principles of the federal civil service laws;

ሐ) የባለሥልጣኑን ዓመታዊ በጀት እና የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል፤ በመንግሥት ሲጸድቅም ይፈጽማል፤

መ) ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል ፤

ሠ) ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ባለሥልጣኑን ይወክላል ፤

ረ) የባለሥልጣኑን የሥራ አፈፃፀምና የፋይናንስ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል።

፫/ ዋና ዳይሬክተሩ ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

c) prepare the annual budget and work program of the Authority and implement same upon approval by the government;

d) effect payments in accordance with the budget and work program approved for the Authority;

e) represent the Authority in its dealings with third parties;

f) prepare and submit to the Ministry performance and financial reports of the Authority.

3/ The Director General may delegate part of his powers and duties to other officials and employees of the Authority to the extent necessary for the efficient performance of the activities of the Authority.

## ፲፪. በጀት

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## 12. Budget

The budget of the Authority shall be allocated by the government.

## ፲፫. የሂሳብ መዛግብት

፩/ ባለሥልጣኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።

፪/ የባለሥልጣኑ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋና ኦዲተሩ ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ።

## 13. Books of Accounts

1/ The Authority shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The books of accounts and financial documents of the Authority shall be audited annually by the Auditor General or by an auditor designated by him.

## ፲፬. ስለመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ

በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር ፹፮/፲፱፻፹፱ ተቋቁሞ የነበረው የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል።

## 14. Transfer of Rights and Obligations

The rights and obligations of the Electricity Agency established under the Electricity Proclamation No. 86/1997 are hereby transferred to the Authority.

፲፭. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፪ሺ፮ዓ.ም

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

15. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of May, 2014.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**